
# የፀሎት ቃልኪዳን ለልጆች



የፍጥረታት አምላክ፣ ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ጸሎታችንን ይሰማል ይመልሳልም። ይህ እንዴት አስደናቂ ነዉ? ኢየሱስ እንዲህ አለ «በሰማይ እና በምድር ያለ ስልጣን ሁሉ ተሰጠኝ» እንግዲህ ሃይል ሁሉ የኢየሱስ ከሆነ፤ ብትፀልዩ ምን ሊፈጠር እንደሚችል ልትገምቱ ትችላላችሁ?

# ፀጋ

በሰማይ ያለህ አባቴ ሆይ ስለወደድከኝ እና ከልጆችህ አንዱ/ዷ ስላደረከኝ አመሠግንሃለሁ።

“ኢየሱስ ሁሉም ሰዎች እግዚአብሄር ምን ያህል እንደሚወዳቸው እንዲያውቁ ስለሚፈልግ ስለ አንድ እረኛ እና ስለጠፋበት በግ ታሪክ ነገራቸው። እረኛው ስለጠፋበት ስለ አንድ በግ እጅግ ተጨንቆ ነበር ስለዚህም ሌሎቹን በጎች ትቶ የጠፋችውን በግ ለማዳን ፍለጋ ወጣ፣ ምክንያቱም ደህንነቷ እንዲጠበቅ ይፈልጋል። በጎች ደካማ ፍጥረቶች ናቸው አንዳንድ ጊዜ ተለይተው ጠፍተው ይሄዳሉ። አደጋ ሊደርስባቸውና በድብ ወይም በአንበሳ ሊበሉ ይችላሉ።”

“የእረኛው ስራ በጎቹን ከአደጋ መጠበቅ ነው፣ እርሱም ይህንኑ ተግባር ነው የፈፀመው። የጠፋውን በግ ሲያገኝ፡ በጣም ደስ ብሎት በክንዱ አቅፎ ወደቤት በማምጣት ደስታውን በታላቅ ድግስ አከበረ!”




**የቃል ጥናት ጥቅስ**

የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን። 1ኛ ዮሐንስ 3:1

“ኢየሱስ ስለእናንተ በጣም ደስ ይለዋል፣ በፍቅሩ ያስደንቃችኋል፣ ስለእናንተ በደስታ ይዘምራል።”

# ፍቅር

## እንድወድህ እና እንድታዘዝህ እርዳኝ።

አብርሃም እግዚአብሄርን ታዘዘ። እርሱም ሚስቱንና የነበራቸዉን ንብረት ይዞ ወደ ሩቅ አገር ሊሄድ ተነሳ። ይህ የአብርሃም መታዘዝ እድሜውን በሙሉ ለሚያደርገው በመታዘዝ፣ በፍቅርና እና በእምነት የማደግ መነሻ ነበር።

አብርሃም እግዚአብሄርን ይወድ ነበር። እርሱ ከብዙ አመታት በፊት ነበር የኖረው። እርሱም ባረጀ ጊዜ እግዚአብሄር እንዲህ አለው “አገርህን፣ ቤተሰቦችህንና ዘመዶችህን ትተህ እኔ ወደማሳይህ ቦታ ሂድ። እባርክሃለሁ ዘርህንም ታላቅ ሕዝብ አደርገዋለሁ። አንተ ለብዙዎች መባረክ ምክንያት ትሆናለህ ታዋቂ ትሆናለህ። በምድር ላይ ያሉ ሁሉ ባንተ ምክንያት ይባረካሉ።

**እግዘአብሄር እንድንታዘዘው ይፈልጋል። እግዚአብሄርን ስንታዘዝ እንደምንወደው እያሳየን ነው ማለት ነው።**




**የቃል ጥናት ጥቅስ**

ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ። ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት። ማቲዎስ 22:37, 38

በጋራ ኢየሱስን መታዘዝ እና መከተል በጣም ደስ የሚያሰኝ ጉዞ ነው!

# ርሕራሔ

አንተ እንደምትወደኝ
ሌሎችን እንድወድ እርዳኝ።

እግዚአብሄር እንደሚወደን አድርገን ሌሎችን መውደድ ማለት ምን ማለት ነው? እስኪ መልሱን እናግኝ። አንድ ሰው ኢየሱስን “ባልንጀራዬ ማን ነው?” ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም ታሪክ በመተረክ ጥያቄዉን መለሰለት። እርሱ በጣም ጉበዝ ታሪክ ተራኪ ነበር።

አንድ ሰው በመንገድ ሲሄድ ሳለ በተደራጁ ወንበዴዎች ጥቃት ደረሰበት፣ ደበደቡት፣ ያለውን በሙሉ ዘረፉት: እንዲሞትም በመንገድ ላይ ጥለውት ሄዱ። ሰዎች በአጠገቡ እያለፉ ይሄዱ ነበር። ምንም አይነት ርሕራሄ አላሳዩትም ነበር። አንድ ሳምራዊ (ሰዎች ዝቅ አድርገው የሚያዩት ሰው ነው) በአጠገቡ በርከክ ብሎ ቁስሉን አጥቦ በጨርቅ በማሰር እና ማገገም ወደሚችልበት ስፍራ በመዉሰድ ረዳዉ በዚያም ሳያበቃ በዚያ መቆየት የሚያስችለውን ገንዘብም ከፈለለት።




ኢየሱስም “እናንተም ለተጐዱ ሰዎች እንዲሁ እንድታደርጉ እፈልጋለሁ” በማለት ታሪኩን ጨረሰ።

**የቃል ጥናት ጥቅስ**

እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት። ዮሐንስ 15:12

እኔ በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባርም መውደድ እፈልጋለሁ።

# ንስሃ

## ስለሃጢያቴ ይቅርታ አድርግልኝ ንፁህ አድርገህ እጠበኝ።

ጴጥሮስ በአንድ ወቅት ኢየሱስን "እኛን የበደለንን ሰው ስንት ጊዜ ነው ይቅር ማለት ያለብን ፡ ሰባት ጊዜ ነውን?" በማለት ጠየቀ። ኢየሱስም "70 x 7" በማለት ከመለሰ በኋላ ሌላ ታሪክ መተረክ ቀጠለ።

በአንድ ወቅት አንድ ንጉስ አገልጋዮቹን ጠርቶ የእርሱ ገንዘብ ምን ያህል እንዳለባቸው ጠየቃቸው። አንድ አገልጋይ ብዙ ብር ነበረበትና መክፈል አልቻለም። ንጉሱ እንዲህ አለው "ያለብህን ገንዘብ እንድትከፍለኝ አንተንና ቤተሰብህን ባሪያዎች አድርጌ እሸጣችኋለሁ!!" አለው። ሰውየው ማልቀስ ጀመረ። ንጉሱ ራራለትና "ከነበረብህ እዳ ነፃ አድርጌሃለሁ" አለው።

ይህ ሰው ከእዳው ነፃ ወጥቶ በመንገድ ሲሄድ ሳለ ከእርሱ ጥቂት ገንዘብ የተበደረ ሌላ ሰው አገኘ እና ካልከፈልከኝ እስር ቤት እንድትገባ አደርግሃለሁ በማለት አስፈራራው። ሰውዬው እባክህ ምህረት አድርግልኝ ብሎ ቢለምነውም ምንም አልራራለትም ወደ እስር ቤት አስገባው።




ይህንን ጉዳይ ንጉሱ ሲሰማ በጣም ተናደደ "አንተ ክፉ አገልገይ እኔ ያንተን እዳ ይቅር አልኩህ አንተ ደግሞ ለአገልጋይህ ይቅር ማለት ያልቻልከው ለምንድን ነው?" በማለት ጮኸበትና ወደ እስር ቤት አስገባው።

### የቃል ጥናት ጥቅስ

ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፥ ከኃጢአቴም አንጻኝ. – መዝሙረ ዳዊት 51:2

**ኢየሱስ እኔን ይቅር ስላለኝ እኔም ሌሎችን ይቅር ማለት እፈልጋለሁ።**

# አምልክ

በሙሉ ልቤ
አመሠግንሃለሁ!

ኢየሱስ በመወለዱ ሰው ሁሉ ደስተኛ ነበረ! መላእክት መጥተው እንዲህ አሉ “ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ። “እረኞችም ሕፃኑን ኢየሱስን ሊጐበኙት እና ሊያመልኩት መጥተው ነበር።




ከረዥም ጊዜ ከ 2000 አመት በፊት ማርያም የምትባል ወጣት ሴትን መልአኩ ገብርኤል ጐብኝቷት ነበር። ለእርሷ የሚያደርሰው ልዩ መልእክት ነበረው። “ማርያም ሆይ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ። እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ። እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥”

## የቃል ጥናት ጥቅስ

አቤቱ፥ በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፥
ተአምራትህንም ሁሉ እነግራለሁ።
– መዝሙረ ዳዊት 9:1

ልክ እንደ ማርያም እንደ ዮሴፍ፣ እንደ እረኞቹ እና ሰብአ ሰገል ኢየሱስን እንዳከበሩት እና እንዳመለኩት እኛም ልናከብረው እና ልናመልከው ይገባናል።

በየቀኑ ላመሰግንህ እፈልጋለሁ!

# መሰጠት

ኢየሱስ ጌታዬ አድርጌ ልከተልህ እፈልጋለሁ።እንደምትፈልገው አድርገህ ለውጠኝ።

ጴጥሮስ ኢየሱስ ያለውን በድንገት አስታወሰና ሮጦ ሄዶ አለቀሰ። ደስ የማይል ስሜት ተሰማው። ኢየሱስ በጴጥሮስ ተስፋ አልቆረጠም። ይቅር ብሎታል ከሞት ከተነሳ በኋላ አብሮት ቁርስ በልቷል። ኢየሱስ ጴጥሮስ የእርሱ ደቀመዝሙር እንዲሆን እና ሌሎች ደቀመዛሙርቶችን እንዲያፈራለት ይፈልግ ነበር። ምንም እንኳን ጴጥሮስ ፍጹም ባይሆንም እንኳን ጌታው አድርጎ ሊከተለው እንደሚፈልግ ኢየሱስ ያውቅ ነበር።




ኢየሱስ ለጴጥሮስ “ዶሮ ከመጮኹ በፊት 3 ጊዜ ትክደኛለህ” ብሎ ነግሮት ነበር። ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት ጥያቄ ሊጠየቅ በታሰረበት ቦታ ጴጥሮስ ይህንን አደረገው። ሰዎች ጴጥሮስን ማስታወስ ሲጀምሩ ፈራ እና ከኢየሱስ ጋር አልነበርኩም በማለት ካደ ከዚያም ዶሮ ጮኸ።

ጴጥሮስ ከዚያ በኋላ ኢየሱስን አልካደም።

**የቃል ጥናት ጥቅስ**

በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ። —ሉቃ 9፡23

ኢየሱስ እኔ ላንተ ሁልጊዜ ታማኝ መሆን እፈልጋለሁ።

# መደገፍ

በመንፈስ ቅዱስህ ሙላኝ።
ለእኔ ያሉህን እቅዶች
ማወቅ እፈልጋለሁ።

ቤተክርስቲያን ተልእኮዋን መፈፀም እንድትጀምር ኢየሱስ መንፈሱን ልኳል። ብዙም ሳይቆይ በአንድ የተወደደ ጴንጤቆስጤ በተባለ ቀን ሃይለኛ ነፋስ ነፍሶ ሁሉም ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ሃይል ተሞሉ።




ኢየሱስ “እናንተ ልትመጡ ወደማትችሉበት ሩቅ ቦታ እሄዳለሁ። አትጨነቁ መንፈሴን ከእናንተ ጋር እንዲሆን እተውላችኋለሁ” አላቸው። ኢየሱስ በመስቀል ከመሞቱና ከሞት ተነስቶ በሰማያት ያለው አባቱ ቀኝ ከመሆኑ በፊት የሆነው ነገር ይህ ነበር። እርሱ ለብቻችን አልተወንም።

አጽናኛችን፣ መምህራችን እና መሪያችን የሆነው የእርሱ መንፈስ ሁልጊዜ አብሮን ነው።

ኢየሱስ በቅዱስ መንፈስህ በመሙላት የበለጠ አንተን እንድመስል አድርገኝ።

**የቃል ጥናት ጥቅስ**

መንፈስ ይሙላባችሁ
– ኤፌሶን 5:18 ሀ

# ተጽኖ

## የፀጋህ፤ የእውነትህ እና የፍትህ መልእክተኛ አድርገኝ።

ኢየሱስ ለፍትህ ልብ ነበረው። ልጆችን ለሚጎዳ ወዮለት ብሎ ተናገረ። እርሱ ሁልጊዜ ይረዳ የነበረዉ ሰዎች ትኩረት የማይሰጧቸውን ልጆችን ጨምሮ፤ የታመሙትን፤ እና ድሆችን ነበር።




ደቀመዛሙርት ኢየሱስን «በመንግስተ ሰማያት ከሁሉ ታላቅ ማነው?» በማለት ጠየቁት፤ ኢየሱስ ስለምን እያሰቡ እንደሆነ ስለሚያውቅ አንድ ትንሽ ልጅ ጠራ። ደቀመዛሙርቱን አይን አይናቸውን እያየ «ልክ እንደዚህ ህፃን ራሱን ዝቅ የሚያደርግ በመንግስተ ሰማያት ታላቅ እርሱ ነው» በማለት እጅግ አስደቂ ነገር ተናገረ።

ኢየሱስ ሌላ አስደናቂ ነገር እንዲህ በማለት ተናገረ “እንደነዚህ ያሉትን በስሜ የሚቀበል እኔን ይቀበላል” ኢየሱስ ይህን ሲል ከልቡ ነበር ምክንያቱም ሁልጊዜ የሚናገረው እውነት ብቻ ነበር።

### የቃል ጥናት ጥቅስ

ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነው ክብሩን አየን። — ዮሐንስ 1:14

እኔም ሁልጊዜ እውነት ለመናገር እሞክራለሁ።

# ደቀመዝሙርነት

**ሌሎችን ወደ አንተ ለመጋበዝና ለክብርህ ተጠቀምብኝ።**

አንድ ቀን ሳውል (ስሙ ጳውሎስ ተብሎ ከመቀየሩ በፊት) በመንገድ እየሄደ ነበር። በድንገት ከሰማይ ታላቅ ብርሃን በርቶ በመሬት ላይ ጣለው። አይኑንም አሳወረው። ከዚያም «ሳውል ለምን ታሳድደኛለህ?» የሚል ድምጽ ሳውል ሰማ። ሳውል አለቀሰ፣ ሳዉልም «ጌታ ሆይ አንተ ማን ነህ?» ብሎ ጮሀ። «እኔ የምታሳድደኝ ኢየሱስ ነኝ» አለው። ጳውሎስ ፈርቶ ይንቀጠቀጥ ነበር። ለሶስት ቀን ያህል ማየት አይችልም ነበር።




ጳውሎስ በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ ትልቅ ስፍራ ያለዉ ሰው ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኙ ብዙ መጽሃፎችን ጽፏል። ነገር ግን ጳውሎስ በአንድ ወቅት ክርስቶስን የማይወድ ጠላት ነበር። የክርስቶስ ተከታዮችን ይገድል ነበር። ነገር ግን ኢየሱስ ለወጠው።

እግዚአብሄር ሳውልን ፈወሰው እና በሄደበት ሁሉ ስለኢየሱስ መስበክ እና ማስተማር ጀመረ። የሳውል ስም በኋላ ጳውሎስ በሚባል ስም ተቀየረ። አለምን ስለኢየሱስ በመስበክና በማስተማር ገለባበጠው፤ ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሰጥ እና ሌሎችም እንደዚያው እንዲያደርጉ ያስተምር ነበር።

## የቃል ጥናት ጥቅስ

እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው። — ማቴዎስ 28:19

**ኢየሱስን እንዲከተሉ ማንን ልጋብዝ እችላለሁ?**

# ስልጣን

በኢየሱስ ስም ፀለይኩ። አሜን።

በርጠሜዎስ አይነስውር ነበረ። በጐዳና ላይ የሚኖር ለማኝ ነበር። ስለኢየሱስ እና ስላደረጋቸው ድንቅ ነገሮች ያውቅ ነበር። ኢየሱስ የታመሙትን፣ አይነስውሮችን ፣ መራመድ የማይችሉትን እንዴት እንደፈወሰ ሰምቶ ነበር። በርጠሜዎስ ወደ ኢየሱስ መርተው እንዲወስዱት እና እርሱንም እንዲፈውሰው ፈልጎ ነበር።

“ኢየሱስ ጌታዬ እባክህ ማረኝ!” በማለት በርጠሜዎስ ጮኸ።

በበርጠሜዎስ ዙሪያ የነበሩት ሰዎች ደግ አልነበሩም “ውይ እስኪ ዝም በል” በማለት ጮኹበት። ነገር ግን በርጠሜዎስ መጮኹን ቀጠለበት። ኢየሱስ ሰማው እና “አምጡት” አለ። በርጠሜዎስ የለበሰውን ጥሎ ወደ ኢየሱስ ሮጠ። “ምን አደርግልህ ዘንድ ትወዳለህ?” በማለት ኢየሱስ ጠየቀው። በርጠሜዎስም “ማየት እፈልጋለሁ” በማለት መለሰ።




በርጠሜዎስ ኢየሱስ ሰዎችን የመፈወስ ሃይል እንዳለው አምኖ ነበር። ለመጀመሪያ ጊዜ የኢየሱስን ፊት በመመልከቱ ምን ያህል ደስ ሊለው እንደሚችል እናንተም ልትገምቱ ትችላላችሁ።

**ኢየሱስ በርጠሜዎስ ወደ እርሱ ሲጮህ ምላሽ ሰጠ፤ ለእናንተም እንደዚሁ ይመልስላችኋል።**

### የቃል ጥናት ጥቅስ

በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ — ፊሊጲሲዮስ 2:9

# የተግባር እርምጃዎች

1. የፀሎት ቃልኪዳኑን ይከልሱ
2. የፀሎት ቃልኪዳኑን ለ 40 ቀናት ይፀልዩ
3. የፀሎት የመጽሃፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በቃልዎት ይያዙ
4. እውነት ወይም ሐሰት የሚለውን አክብቡ እና በመልሶቻችሁ ላይ ተወያዩ

| | |
|---|---|
| የእግዚአብሔር ፀጋ የተወደደ/ደች ልጅ አድርጐኛል። | እውነት ሐሰት |
| መታዘዝ በረከትን ያስከትላል። | እውነት ሐሰት |
| የሚወዱንን ብቻ ነው መውደድ ያለብን። | እውነት ሐሰት |
| ኢየሱስ ሌሎችን ይቅር እንድንል እና ቂም እንዳንይዝ ይፈልጋል። | እውነት ሐሰት |
| ደስ ባለን ጊዜ ብቻ ነው እግዚአብሔርን ማመስገን ያለብን። | እውነት ሐሰት |
| ኢየሱስን ለመከተል ስንወስን እርሱን እንድንመስል ያደርገናል። | እውነት ሐሰት |
| መንፈስ ቅዱስ መሪያችን ነው። ኢየሱስ ለልጆች ጊዜ አልነበረውም። | እውነት ሐሰት |
| እግዚአብሔር ለሌሎች ስለኢየሱስ ለመናገር የሚጠቀመው ጐልማሶችን ብቻ ነው። | እውነት ሐሰት |
| በሰማይ እና በምድር ሁሉ ያለ ሃይል ሁሉ የእግዚአብሔር ነው። | እውነት ሐሰት |
| ፀሎት ሃይል ነው ምክንያቱም በኢየሱስ ስም ውስጥ ሃይል አለ። | እውነት ሐሰት |
| እግዚአብሔር ስፀልይ ይሰማኛል። | እውነት ሐሰት |



# የፀሎት ቃልኪዳንን እንዴት እንደምንፀልይ

**ደረጃ 1** ፀሎቱን ለራሳችሁ በየቀኑ ለ10 ቀናት ያህል ፀልዩ።

**ደረጃ 2** ፀሎቱን ስትፀልዩ ለፀሎት ቃልኪዳን ማንን መጋበዝ እንዳለባችሁ እንዲያሳያችሁ ኢየሱስን ጠይቁ።

**ደረጃ 3** እናንተም ለዚያ ሰዉ እየጸለያችሁ ያ ሰዉ ለእናንተ ፀሎቱን ለ40 ቀናት ያህል ለእናንተ እንዲጸልይ ጋብዙት። ያ ሰዉ ጓደኛችሁ፣ እናታችሁ፣ አባታችሁ፣ እህታችሁ፣ ወንድማችሁ፣ አያታችሁ፣ አስተማሪያችሁ ወይም የቤተክርስቲያን መጋቢያችሁ ሊሆን ይችላል።

**ደረጃ 4** ከፀሎት አጋራችሁ ጋር እግዚአብሄር ፀሎታችሁን የመለሰበትን ሁኔታ ተከፋፈሉ። ልትጽፉት ወይም በስእል ልታሰፍሩት ትችላላችሁ።

**ደረጃ 5** የተመደበውን የቃል ጥናት ጥቅስ በቃላችሁ ያዙ።

**ደረጃ 6** የኢየሱስን የምስራች ከሌሎች ጋር ተከፋፈሉ።

**ደረጃ 7** ከላይ ያሉትን ደረጃዎች ኢየሱስን በጋራ ለመከተል ከተስማሙ አዲስ የፀሎት አጋሮች/ጓደኞች ጋር ይድገሟቸው።

የእኔ ስም: ______________________________

ዛሬ የልጆች ፀሎት ቃልኪዳን መፀለይ ጀምሬያለሁ።

የዛሬው ቀን : __________________

የፀሎት አጋሬ:

______________ ስም ________ ቀን

______________ ስም ________ ቀን

______________ ስም ________ ቀን

# የፀሎት ቃልኪዳን ለልጆች

| | |
|---|---|
| **ፀጋ** | በሰማይ ያለህ አባቴ ሆይ ከልጆችህ አንዷ/ዱ ስላደረከኝ አመሠግንሃለሁ። |
| **ፍቅር** | እንድወድህ እና እንድታዘዝህ እርዳኝ። |
| **ርሕራሔ** | አንተ እንደምትወደኝ ሌሎችን እንድወድ እርዳኝ። |
| **ንስሃ** | ስለሃጢያቴ ይቅርታ አድርግልኝ ንፁህ አድርገህ እጠበኝ። |
| **አምልኮ** | በሙሉ ልቤ አመሠግንሃለሁ! |
| **መሰጠት** | ኢየሱስ ጌታዬ አድርጌ ልከተልህ እፈልጋለሁ። እንደምትፈልገው አድርገህ ለውጠኝ። |
| **መደገፍ** | በመንፈስ ቅዱስህ ሙላኝ። ለእኔ ያሉህን እቅዶች ማወቅ እፈልጋለሁ። |
| **ተጽኖ** | የፀጋህ፣ የእውነትህ እና የፍትህ መልእክተኛ አድርገኝ። |
| **ደቀመዝሙርነት** | ሌሎችን ወደ አንተ ለመጋበዝና ለክብርህ ተጠቀምብኝ |
| **ስልጣን** | በኢየሱስ ስም ፀለይኩ አሜን |

The PRAYER COVENANT For Children! | EveryHome for Christ | FIND US ON YouVersion | 4/14 window movement

ኤቭሪ ሆም ፎር ክራይስት የኢየሱስን የምስራች በምድር ላይ በሁሉም ቤቶች ውስጥ እ.ኤ.አ ከ 2039 በፊት ለማካፈል ቆርጦ የተነሳ አለም አቀፍ ድርጅት ነው። ከድርጅቱ ጋር በኢንተርኔት OIKOS.global መገናኘት ይችላሉ፡።

የቅጂ መብት © 2017 ዊክሊፍ ቶጐ/ካንዲ ማራቦሊ። መብቱ የተጠበቀ ነው። ስእል ሉክ ፍላወርስ። የልጆች የፀሎት ቃልኪዳን ከ የፀሎት ቃልኪዳን ሃይል ለልጆች ከሚለው የካንዲ ማራቦሊ እና ስቴፈን አይር ስራ የተዛመደ ነው። theprayercovenant.org/Children